http://www.kinijitethiopia.org

e-mail kil@kinijitinternational.org Voice Mail/Fax 1-206-203-3974


**ጋዜጣዊ መግለጫ**

**ኪል-009/07**
**መጋቢት 26 ቀን፣ 1999**

## ምን ታደርጉኛላችሁ በሚል እብሪት ፍትህን እየፈነገጠ መሄድ የማይችል መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ በትግሉ ለወያኔ ያረጋግጣል::

መጋቢት 26 1999 አ.ም ወያኔ በቅንጅት መሪዎች ላይ በእብሪት የተሞላውን እኩይ ፍላጎቱን በዳኝነት ስም ባስቀመጣቸው ካድሬዎቹ አማካይነት ፈጽሟል:: ይህ ብይን የቅንጅት መሪዎችን ወያኔ በሞት ወይም በእድሜ ልክ እስራት ለመቅጣት ቆርጦ መነሳቱን የሚያሳይ ነው:: የተሰጠው የእብሪት ብይን በጥቂት የቅንጀት መሪዎች በሆኑ ግለሰቦች ላይ ብቻ አይደለም:: ውሳኔው የአትዮጵያ ህዝብ ለፍትህ፣ ለነጻነት፣ ለህገመንግስታዊ ስርአት፣ ለዴሞክራሲ መስፈን ባለው ቅን ህልም ላይ የተሰነዘረ ጥቃት ነው:: ከድህነት፣ ከበሽታና ከመሃይምነት ራሱን ለማውጣት፣ ብሄራዊ ጥቅሙን፣ ደህንነቱን፣ ህልውናውን ለማስከበር ባሳየው ቁርጠኛነት ላይ የታወጀ ጦርነት ነው:: በአርበኛነት፣በሃገር ወዳድነትና ለህዝብ ተቆርቋሪነት ላይ የተወሰደ የበቀል እርምጃ ነው:: ዘራፊነትንና ሙስናን፣ ዘረኛነትንንና ከፋፋይነት በሚቃወመው ለአንድነቱ ቀናኢ በሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የተጣለ የእብሪት የመከራ ቋጥኝ ነው::

ምርጫ ያጭበረበረው ወያኔ፣ የዘር ማጥፋት እቅድ የነበረው ወያኔ፣ ሃገር የካደው ወያኔ፣ የመሰብበሰብ፣ የመጻፍ፣ የመናገርና የመደራጀት ህገ መንግስታዊ መብቶችን የጣሰው ወያኔ፣ ሰላማዊ ዜጎችን ለመጨፍጨፉ በገዛ ኣጣሪዎቹ ማስረጃ የቀረበበት ወያኔ፣ የሃገር ሃብት እንዳሻው የሚዘርፈው ወያኔ፣ የሃገሪቱን ክብርና የዘለቄታ ጥቅም ለስልጣንና ለነዋይ ሲል በአደባባይ የሚሸጠው ወያኔ መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅቆ ያውቀዋል:: የቅንጅት መሪዎችም ሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ በእዚህ ደረጃ ወንጀሉ የበዛ የፖለቲካ ድርጅት አምባገነንነት በነገሰበት ሃገር ላይ እውነተኛ ፍትህና ፍርድ የማይገኝ እንደሆነ ጠንቅቀው የሚያውቁት በመሆኑ በዛሬው የወያኔ ፍርድ ቤት ብይን የሚደናገጡ እንዳልሆኑም ይታወቃል::

የወያኔንን የፖለቲካ ትዕዛዝ ለማስፈጸም ሲሉ፣ ፍትህንና ህሊናን የሚያክል ነገር ለሆዳቸው የማይሸጡ ዳኞችና የፍትህ ስርአት ያለባት ኢትዮጵያ ብትሆን ኖሮ፣ ምርጫውም ተጭበርብሮ አይቀርም ነበር:: ወያኔም በእብሪት ንጹሃን ዜጎች አይጨፈጭፍም:: አንድም ግለሰብ ያለአግባብ በሃሰት ተወንጅሎ ለአመታት አይደለም ለአንድም ቀን በእስር አያድርም ነበር::

ከማንም በላይ እንዲህ አይነቱ የፍትህ ስርአት የሌለበት ሃገር መሆኑን የሚያውቁት የቅንጅት መሪዎች በእዚህ ፍትህ ፈንግጥ የወያኔ ካድሬዎች ውሳኔ መደናገጥ ቀርቶ የሚገረሙም አይሆኑም:: በሃገራችን ፍትህ አልባ ስርአት መንገሱን በመረዳት ነው የቅንጀት መሪዎች በሃገራችን መቋቋም ከሚገባቸው ነጻ ተቋማት መሃል ዋንኛው የፍትህ ተቋሙ ነው በማለት ባገኙት አጋጣሚ የወተወቱት:: የህዝቡን የፍትህ ጥማት ለማርካት፣ በቅድሚያ በምርጫ ማኒፌስቶ፣ ቀጥሎም በሃገሪቱ የዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ እንዲሳካ የነጻ የፍትህ ስርአትና በነጻ ህሊናቸው የሚፈርዱ ዳኞች ማስፈለጋቸውን ሳይታክቱ የገለጹት:: የዛሬዎቹ ብይን ሠጪዎች ህሊናቸውንና ሰብዕናቸውን በጊዜያዊ ጥቅም ብል አስበልተው በሰው ቀፎነታቸው ለብይን ባይቀመጡ ኖሮ የቅንጀት መሪዎችና የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል እነሱንም ከህሊና ባርነት ነጻ ለማውጣት የተነሳ መሆኑን አይስቱትም ነበር::

ወያኔ ፍርድ ቤቱን የፖለቲካ ፓርቲው ሌላ ክፍል አድርጎ፣ በካድሬ ዳኞቹ ትብብር በህዝብና በሃገር ላይ የፈጸመው ወንጀል አላማው በሃገሪቱ ምንም አይነት የፖለቲካ ተቃውሞ እንዳይኖር ለማድረግ ነው:: የወያኔ ገዥዎች እንዳሻቸው ሲገድሉና ሲያስገድሉ፣ ሲያስሩና ሲዘርፉ፣ ያገር ጥቅምና አንድነትን ሲንዱ ተው የሚላቸው ብሄራዊ ጀግና እንዳይኖር ለማድረግ ነው:: የፖለቲካ ተቃውሞው የወያኔ ገዠዎች ከገደቡለት አጥር ውጭ ወጥቶ ስለህዝብ መበደል፣ መገፋት፣ መደህየትና ስለሀገር መዋረድ እንዳይናገር ለማድረግ ነው::


**Kinijit International Political Leadership Secretariat,**
**P.O.Box 14701**
**Silver Spring MD, 20911 USA**
**Fax / Voice Mail. +1-206-203-3974** **www.kinijitethiopia.org**

ቅንጅት እነዚህን ሁሉ የህዝብና የሃገር በደሎች ይፋ ወጥተው የተነገሩበት ዋንኛው ልሳን መሆኑንን ወያኔ ያውቀዋል:: ይህ ብቻ አይደለም ለእነዚህ የአገዛዙ በደሎች ፈውስ ያለው ድርጅት መሆኑንና ህዝብ ያመነው ድርጅት መሆኑንም ወያኔ ያውቃዋል:: ወያኔ አሁንም ያላወቀውና ያልተረዳው የቅንጅት መሪዎች ቁርጠኛነት የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ ቁርጠኛነት፣ ምኞታቸውና ህልማቸውም የህዝቡ ምኞትና ህልም መሆኑን ነው::

ወያኔ የቅንጅት መሪዎችን ለማስፈራራት፣ ለማግባባትና በእርቅ ሰም ለማጭበርበር ያደረገው ሙከራ ሁሉ በመሪዎቹ የእምነት ጽናት የትም እንደማያደርሰው ባወቀበት የመጨረሻው ሰአት ማንንም ማሞኘት በማይችልበት የህግ ስም በኢትዮጵያ ህዝብ ብርቅየ ንጹሃን ልጆች ላይ የፍርድ የጭቃ ጅራፉን አሳርፏል:: ወያኔ ያዋጣኛል ያለውን ግፍ ፈጽሟል:: ከእንግዲህ የነጻነት፣ የዴሞክራሲና የፍትህ ጥማት የጥቂት የቅንጅት መሪዎቹ ፍላጎት ብቻ እንዳልሆነ ማሳየት የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪካዊ ሃላፊነት ነው:: በቅንጅት መሪዎቻችን ላይ የተሰጠው ብይን በሰባ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ህዝብ የነጻነትና የፍትህ ጥማት ላይ የተጣለ የጭቆና ማእቀብና በአገር ላይ የተቃጣ የጥፋት ተልዕኮ ነው ::

መጋቢት 27 1999 አመተ-ምህረትም ከቅንጅት መሪዎች ያልተለየ እጣ የሚጠብቃቸውን ጋዜጠኞች የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን ከወያኔ እስር ቤት ማውጣት ብቻ ሳይሆን፣ የታሰሩለትንና የተሰቃዩለትን የነጻነትና የፍትህ ጥያቄ መልስ ማስገኘት ያለበት መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቀዋል:: ወያኔን ከመሰለ የነጻነትና የፍትህ ጠር ጋር የሚደረግ ትግል ረጅምና መራራ እንደሆነ ጠንቅቆ ይረዳዋል ::

ለዚህ ዕልህ አስጨራሽ የነጻነት ተጋድሎ ይበልጥ ሀሞቱን አስቆጥቶ፣ ወገቡን ጠበቅ አድርጎና አንድነቱን አጽንቶ፣ በእብሪት የሰላምንና የእርቅን ጥሪ እየረገጡና ፍትህን እየፈነገጡ ለረጅም አመታት በገዥነት መቆየት እንደማይቻል ለወያኔ መሪዎችና ለጀሌዎቻቸው የኢትዮጵያ ህዝብ ማረጋገጥ ይገባዋል::

ይህ የዛሬው በእብሪት የተሰጠ ብይን ከሁሉም በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ ከሚገኙ ኢትዮጵያዊ ዜጎች፣ ፖለቲካና ፖለቲካዊ ካልሆኑ ድርጅቶች አባላት መሰረታዊ የፍትህ ስሜት ጋር የሚጋጭ ነው:: በመሆኑም በሃገራችን ዘላቂ ሰላምና የዴሞከራሲ ስርዓት ግንባታ ላይ ያነጣጠረውን የወያኔን ጥቃት የጋራ ጥቃታቻን አድርገን በአንድነት እንድንቀሳቀስ ከመቼውም በላይ ያስገነዘበ ኩነት ነው:: በጥቂት አምባገነኖችና ለሆዳቸው ባደሩ ጀሌዎቻቸው አማካይነት የነጻነትና የዴሞክራሲ ትግል ጥማት በሀሳዊ ፍትህ ስም ተዳፍኖ መቅረት እንደማይችል ለወያኔ ለማሳየት በጋራ መነሳት የወቅቱ የዜጎች ሁሉ ታሪካዊ ግዴታ ነው ::

የነጻነትና የፍትህ መብቶች የተፈጥሮ የሰብኣዊና የዜግነት መብቶች ናቸው:: እነዚህን መብቶች በጠብመንጃ ሃይል አፍነው ለማጥፋት የሞከሩት ሁሉ መውደቂያቸው ከታሪክ ትቢያ ላይ ነው:: ፍትህን እየጨፈለቁ መጓዝን የመረጡት የኢትዮጵያ አምባገነኖችም ዕጣ ከዚህ የተለየ እንደማይሆን አንጠራጠርም::

ፍትህ ለሰፈነባት ኢትዮጵያ መገንባት ሁሉም የድርሻውን ይወጣ!!

**ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ**

**Kinijit International Political Leadership Secretariat,**
**P.O.Box 14701**
**Silver Spring MD, 20911 USA**
**Fax / Voice Mail. +1-206-203-3974** **www.kinijitethiopia.org**